በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን ዓላማ እንወቅ

## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## መስከረም ፮ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# መግቢያ

- በሕይወቱ ግብ የሌለው ሰው ይወድቃል፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ግብ እንዲኖረን ያስፈልጋል፡፡

- እንግዲህ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለው ዓላማና ፈቃድ ምንድር ነው? ስለምን ፈጠረን? እርሱ ለእኛ ያለውን ዕቅድ በምን እናውቃለን?

- እግዚአብሔር ውዳጆቹ ሆነን ከርሱ የሚናገኘውን ሰላምና ነጻነት ፈጽመን እንድናውቅ ስለሚሻ ዘወትር ያነጋግረናል፤ ይወደናልም፡፡ እርሱን ማወቃችንም ኃጢአትን እንድንጠላ ያደርገናል፡፡

- እግዚአብሔር በምንኖረው ኑሮ ለእያንዳንዳችን ሕይወት ያለውን ዕቅድ ለማወቅ የሚከተሉትን መንገዶች እንከተል፡፡

1. <u>*የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተን እንቀበል*</u>

- እግዚአብሔር እኛን የሚያነጋግርባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፡፡ የሚከተሉትም ተጠቃሽ ናቸው፡፡
    1. ቅዱሳት መጻሕፍት፡- የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅባቸው የማዕዘን ድንጋዮች ናቸው፡፡
    2. መንፈስቅዱስና ጸሎት፡- በውስጣችን ያለ መንፈስቅዱስ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ ልባችንን በመክፈት ይመራናል፡፡ “ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል፡፡” <u>*ዮሐ 16፡13 እና 14፡26፡፡*</u>
    3. ከእግዚአብሔር የሆነ ምክር፡- ከቀሳውስት ወይም በሳል ከሆኑ ክርስቲያኖች ጋር የምናደርገው ውይይት የተለያዩ አማራጮችን ጉዳትና ጥቅም ያስረዳናል፡፡ “አሳብ በምክር ትጸናለች፥ በመልካምም ምክር ሰልፍ አድርግ፡፡” <u>*ምሳሌ 20፡18፤*</u> “በመልካም ሥርዓት ሰልፍ ታደርጋለህ ድልም ብዙ ምክር ባለበት ዘንድ ነው፡፡” <u>*ምሳሌ 24፡6፤*</u> “ሽቱና ዕጣን ልብን ደስ ያሰኛሉ እንዲሁ ነፍስ በወዳጁ ምክር ደስ ይላታል፡፡” <u>*ምሳሌ 27፡9፡፡*</u>

# እቅዱን እንወቅ…

4. አጋጣሚዎች፡- እነዚህም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምመውቅባቸው መጠቆሚያዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
5. ኅሊናችን፡- የነቃ ኅሊና ትክክለኛና ቁርጥ ውሳኔዎችን ለመወሰን መልካም መሪነው፡፡

## *2. የእግዚአብሔርን ድምጽ ለይን እንወቅ*

- እግዚአብሔር ሲናገር መልእክቱ እውነተኛ እንደሆነ እርግጠኞች ነን፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ መወላወል የሌለበት፤ ባሕርዩም የማይለወጥ ቃል እንደገባልን የሚፈጽምልን አምላካችን ነው፡፡

- የእግዚአብሔርን መልዕክት ለማወቅ ዌወም ለመረዳት በቃሉ አማካኝነት ብቻችንን ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት ጊዜ ይኑረን፡፡

- ስለምንቀበላቸው መልዕክተናች እርግጠኛ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል፡፡
    - የወሰንነው ውሳኔ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ስምምነት አለው?
    - የወሰንነው ውሳኔ ጥበብን የተሞላ ውሳኔ ነውን?
    - ስለጉዳዩ እንጸልያለን?
    - የንስሐ አባታችን በውሳኔአችን ይስማማሉ?
    - እንደፈቃዱ የምንሻውን ይሰጠን ዘንድ እንጠይቀዋለን?
    - ስለ ጉዳዩ እውነተኛ ሰላም አለን?
    - በእግዚአብሔር እና ከሆነው ጋር መስማማት አለው?
    - እግዚአብሔር በሕይወታችን ካለው አጠቃላይ ዓላማ ጋር ስምምነት አለው?
    - ይህን ውሳኔ ብወስን እግዚአብሔርን አከብርበታለሁ?

# እቅዱን እንወቅ…

## *3. የእግዚአብሔርን መልእክት እንቀበል*

- የእግዚአብሔርን መልእክት ለመቀበል አስቀድመን እግዚአብሔርን ለመስማት ዝግጁ መሆን ይኖርብናል። እግዚአብሔርን የማንሰማ ከሆንን ምክንያቱን ማወቅ ይገባናል።

- የእግዚአብሔርን ዕቅድ ከመቀበል የሚያግዱን በርካታ ድክመቶች አሉ። የሚከተሉትም እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ።
  - *በበርካታ ሥራዎች መጠመድ፡-* እግዚአብሔርን መስማት ያስችለን ዘንድ ጸጥ ያለ የጽሙና ጊዜ ያስፈልገናል። “ሲሄዱም እርሱ ወደ አንዲት መንደር ገባ፤ ማርታ የተባለች አንዲት ሴትም በቤትዋ ተቀበለችው። ለእርስዋም ማርያም የምትባል እኅት ነበረቻት፥ እርስዋም ደግሞ ቃሉን ልትሰማ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጣ ነበረች። ማርታ ግን አገልግሎት ስለ በዛባት ባከነች፤ ቀርባም። ጌታ ሆይ፥ እኔ እንድሠራ እኅቴ ብቻዬን ስትተወኝ አይገድህምን? እንኪያስ እንድታግዘኝ ንገራት አለችው።” *ሉቃስ 10፡38-40*፤ “የእስራኤል ቅዱስ፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና። በመመለስና በማረፍ ትድናላችሁ በጸጥታና በመታመን ኃይል ይሆንላችኋል እናንተም እንቢ አላችሁ።” *ኢሳ 30፡15።*

  - *የእግዚአብሔርን ፈቃድ ወይም ሐሳብ ያለማወቅ*- የምንኖረው በርካታ ባሕላዊ ተጽእኖዎች ባሉበት ዓለም ውስጥ ስለሆነ በሕይወታችን ትክክለኛ ምርጫዎችን መምረጥ የሚያስችሉን የእግዚአብሔርን ኃይልና ጥበብ ያስፈልጉናል።

  - *የሌሎች ተጽእኖ፡-* ጓደኞቻችነ ዘወትር በርካታ ምክሮችን ይሰጡናል፤ ነገር ግን ምክሮቻቸው የእግዚአብሔርን ፈቃድ የተከተሉ ናቸውን?

  - *አልጠቅምም ብሎ ማሰብ፡-* ምንም ነገር እንደማመመገባን ሆነን ይሰማናል። የሊቀ ነቢያት ሙሴንና *ዘጸ 3፡10-11* እና የጌዴዎንን ታሪክ *መሳ 6፡12-15* እናንብብ።

  - *ጥራጣሬ፡-* እግዚአብሔር ወደ በጎው ሁሉ ሊመራን እንደሚችል ማማን ይገባናል። “ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።” *ዕብ 11፡6።*

# እቅዱን እንወቅ…

- *የተሳሳቱ አነሳሽ ምክንያቶች፡-* የተሳሳቱ አነሳሽ ምክንያቶች ካሉን እግዚአብሔር ጸሎታችንን አይሰማም፡፡ “ትለምናላችሁ፥ በምቾቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም፡፡” *ያዕ 4፡3*፤
- *ፍርሐት፡-* እግዚአብሔር እናደርገው ዘንድ የሚፈልገውን ለመሥራት ወይም ለማድረግ መፍራት ቄወም እሳሳታለሁ… ብሎ መፍራት፡፡
- *የራሳችን ፈቃድ፡-* እግዚአብሔር ይመራን ዘንድ ሳንጠብቀው ማድረግ የምንፈልገውን አስቀድመን መወሰናችን፡፡
- *በፈቃዳችን አውቀን የምንሠራው ኃጢአት፡-* በሕይወታችን ለእግዚአብሔር የማንታመንባቸው አውቀን ኃጢአት የምንሠራባቸው ገጽታዎች መኖራቸው፡፡
- *መልካም ዕድሎችን ማሳለፍ፡-* እግዚአብሔር ለጸሎታችን መልስ እንዲሰጠን የምንሻ ከሆንን ለሚሰጠን ዕድሎች ሁሉ አእምሮአችን ነቅቶ ጠባቂ መሆን አለበት፡፡

## *4. እርሱ እየመራን እኛ እንከተለው*

- እግዚአብሔር ሲናገረን በሚመራን አቅጣጫ ለመሄድ መፈለግ አለመፈለጋችንን መወሰን ይኖርብናል፡፡ እግዚአብሔር የሚመክረን ሕይወታችንን ለማወክ ሳይሆን በማያልቅ ፍቅሩ ሥር ሆነን በመደላደል እንድንኖር ነው፡፡ “አባት ከሆናችሁ ከእናንተ ከማንኛችሁም ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ደግሞ ቢለምነው በዓሣ ፋንታ እባብ ይሰጠዋልን? ወይስ እንቁላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?”*ሉቃ 11፡11-13*
- እግዚአብሔር መንፈስቅዱስን የላከው መሪያችንና አስተማሪያችን እንዲሆን ነው፡፡ “አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል፡፡” *ዮሐ 14፡26፤ ዮሐ 16፡7-13፡፡*

*ማጠቃለያ*

- እግዚአብሔርን መስማት የምንማረው በቀላሉ ስብከቶችን በመስማት አይደለም የተማርነውን በማድረግ እንጂ፡፡ እግዚአብሔርን መስማትን መማር ድምጹንም ማወቅ ይኖርብናል፡፡
- እግዚአብሔር በሕይወታችን ያለውን ዕቅድና ዓላማ በየደረጃው እንጂ በአንድ ጊዜ የማይገልጥ መሆኑን እንወቅ፡፡
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ በአንድ ቀን ሊከሰት አይችልምና ትዕግሥተኞች ሆነን ሲመራን እንከተለው፡፡
- እግዚአብሔር ከተናገረ የምንገኘው የት፤ በምን ሁኔታ እንደሆነ ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡

# የጥያቄ መልስ

*ጥያቄ፦* ካህናትን የማክበር ክርስቲያናዊ ግዴታ አለብን?

## *ለካህናት የሚገባ ክብር - ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ 2ኛ ጢሞ 2፡12 ተርጉሞ እንዳስተማረው*

- ማንም ካህናትን የሚያከብር ቢኖር እግዚአብሔርን ያከብራል። ካህናትን መናቅና መዝለፍንም የተማረ ቀስ በቀስ እግዚአብሔርንም ወደ መስደብ ደረጃ ይደርሳል። "እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።" *ማቴ 10፡40።* #እግዚአብሔርን ፍራው የሚያገለግለውን ካህኑን አክብረው፤*ሲራክ 7፡31።*

- አይሁድ ሙሴን በመናቅና በመሳደባቸው በድንጋይም ሊወግሩት በመፈለጋቸው የተነሳ በእግዚአብሔርም ሲያጉረመርሙና እግዚአብሔርንም ሲያሙ ተገኝተዋል። "ሙሴም፦ ሊወግሩኝ ቀርበዋልና በዚህ ሕዝብ ምን ላድርግ? ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።" ዘጸ 17፡4። አንድ ሰው በካህናት ላይ በትህትናና በፍቅር ሳይሆን በድፍረት የሚናገር ክፉንም የሚያደርግ ከሆነ በእግዚአብሔር ላይም የባሰ እንደሚሆን እንረዳ።

- ካህኑ በደለኛ ሆኖ ብንንቀው እንኳ ካህኑን ከማክበርም ተመልሰናልና እግዚአብሔር ይመለከተናል። "ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል።" *ማቴ 10፡40*፤ "ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል። ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም፥ ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ።" *ማቴ 23፡2-3።* ተብሎ ተጽፎልናልና።

- ክህኑን የምንንቀው ከሆንን የናቅነው እሱን ሳይሆን የቀባውን እግዚአብሔርን ነው። በማይገባው አገልጋይም ቢሆን በጥምቀት ልጅነት፤ በንስሐ የኃጢአት ሥርየት እንደሚሰጠን እንወቅ።

- እግዚአብሔር በደካማውም ባሪያም ቢሆን ሕዝቡ ይድኑ ዘንድ ሥራውን ይሠራል። ለሕዝቡ ሲል በአህያና በበደለናው በበለዓም ከተናገረ በካህናትማ እንዴት አድርጎ ይናገር ይሆን። *ዘኁ 22፡21።* *ቀዳ ሳሙ 2፡1 እስከ ምዕራፍ 3፡21* ም የሚያስተምረን ይኸንኑ ነው።

ይቆየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

መልካም አዲስ ዓመት
ይሁንልን።